# እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

## ጥያቄ፦መንፈሰ ቅዱስ ማን ነው?

መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ ነው። መንፈሰ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አካልና ፍጹም ገጽ ያለው ነው። መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ በአካልና በገጽ ፍጹም ሲሆን በባሕርይና በመለኮትፈቃድና በሥልጣን ከአብና ከወልድ ጋር አንድ ነው። እንደ አብና እንደ ወልድም እግዚአብሔር ነው። መንፈስ ቅዱስ በባሕርይና በመለኮት ከአብና ከወልድ ጋር አንድ በመሆኑ ሁል ጊዜ ከአብና ከወልድ ጋር አንዲት ስግደት አንድ ምስጋና የሚቀርብለት ፍጹም አምላክ ነው።

ሦስቱ አካላት አብ ወልድ መንፈሰ ቅዱስ በባሕርይና በመለኮት አንድ በመሆናቸው ሦስቱም እግዚአብሔር ይባላሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር አብ፤ እግዚአብሔር ወልድ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ። ነገር ግን ሦስቱ አካላት አንድ አምላክ፤ አንድ ፈጣሪ፤ አንድ እግዚአብሔር ይባላሉ እንጂ ሦስት አማልክት፤ ሦስትፈጣሪ፤ ሦስት እግዚአብሔር አይባሉም።

## ጥያቄ፦መንፈሰ ቅዱስ የማን እስትንፋስ ነው?

«በምስጢረ ኵነት» መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ እስትንፋስ ነው። አብ የወልድና የመንፈሰ ቅዱስ ልብ (ልቡና) እንደሚባል ወልድም የአብና የመንፈሰ ቅዱስ ቃል እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም የአብና የወልድ እስትንፋስ ነው።

«ሁሉን የሚመላ፤ የሚቃኝ፤ በሁሉ ያለ፤ ሳይታይ በሁሉ የሚያድር፤ የአብ የወልድ እስትንፋስ በሚሆን በሚያድን በመንፈሰ ቅዱስ እናምናለን» ሲል ቅዱስ አትናትዎስ ዘእስክንድርያ አስረድቷል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ ፹፬)።

ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያም ሰለ መንፈስ ቅዱሰ አምላክነት፣ ስለ ሀብቱ ለመግለጽ በጻፈው መልእክቱ እንዲህብሏል። «አብ ወልድ ባሉበት ቦታ በዚያ መንፈስ ቅዱስን እናስተውላለን (እናየዋለን)፤ በአብ በወልድ ያለ የአምላክነት ክብር ለመንፈስ ቅዱስ ገንዘብ ነው። ይኸውም ቸርነት፣ ይቅርታ፣ እውቀት፣ ቅድስና፣ ሕይወት፣ ንጽህና ነው። (ሃይማኖተ አበው ገጽ ፺፲፬)።

ቀጥሎም ይህ ቅዱስ መምህር ስለ መንፈስ ቅዱስ የጻፈውን እንመልከት። «ሰለ እርሱ (ስለ መንፈሰ ቅዱስ) በተናገርነው ነገር የተጨመረ የለበትም፤ አልተቀነሰለትምም። ነገር ግን ነበልባል ከእሳት እንደማይለይ፤ ፀዳልም ከብርሃን እንደማይለይ፤ እንዲሁም ንጽህና፤ ሕይወት፣ ቸርነት፤ እውቀት፤ ከመንፈስ ቅዱስ አይለይም። መንፈስ ቅዱስም ጥንት ፍጻሜ በሌላቸው በአብ በወልድ ህልው ነው። ከብዙዎችም ጋር አይቆጠርም፤ ሦስቱ አካላት በባሕርየ መለኮት አንድ እንደሆነ፤ ከብዙዎች ጋር እንዳይነጻጸር አታውቁምን? አብ አንድ እንደሆነ ወልድም አንድ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም አንድ ነው።» (ሃይማኖተ አበው ገጽ 114 ቍ. 42-44)።

መንፈስ ቅዱስ በአካሉና በገጽ ህልው ሆኖ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ባሕርይ በአንድ መለኮት አንድ አምላክ በመሆኑ በከዊን እስትንፋስነቱ የአብና የወልድ እስትንፋስ መሆኑን ቅዱስ ባስልዮስ ሲመሰክር «በሁሉ በምልአት የሚኖር ይህ መንፈስ ቅዱስ ነው። በሚያምንበት በአንዱም (በእያንዳንዱ) ሁሉ ላይ እርሱ ሁለንተናው (ፍጹም አካሉ) ይኖራል። እርሱ ሁለንተናው በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ ህልው ነው፤ እስትንፋሳቸው ነው» ብሎአል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ 116 ቍ 57)።

ዮልዮስ (አቡሊዲስ) ሊቀ ጳጳስ ዘሮሜም መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ እስትንፋስ እንደሆነ ሲያስረዳ «አብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው (መገኛቸው) ነው። ወልድም ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው ነው። በዚሁም የ ሦስቱ አካላት መለኮት አንድ እንደሆነ አውቀን ለእርሱ እንስግዳለን» ብሎአል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ 138 ቍ. 8)።

ሦስት አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በየአካላቸው በፍጹምነት ህልዋን ሆነው በአንድ ባህርይና በአንድ መለኮት በአንድ ጌትነት አንድ አምላክ መሆናቸውን በመግለጽ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ የጻፈውን እንመልከት። «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአካል ሦስት በባሕርይ አንድ ነው ብሎ ማመን ይህ ነው። የማይመረመረው በቅድምና የነበረ መንፈስ ቅዱስም በገጽ በአካሉ ፍጽም ነው። ሐዋርያት ያስተማሩት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተቀበለቻቸው ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተናገሩት» (ሃይማኖተ አበው ገጽ 256 ቍ. 14-16)።

«አካላዊ ቃልን በመለኮቱ ከመንፈስ ቅዱስ ክብርን ተቀበለ (አገኘ) የሚለው የመናፍቃን አባባል በመቃወም ቅዱስ ቄርሎስ ሲጽፍ መንፈስ ቅዱስ የአብን የወልድ እስትንፈስ መሆኑን እንዲህ ሲል አስረድቶአል። «ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ምንም ምን ክብር ይቀበል ዘንድ ወደደ እንል ዘንድ የአብ እስትንፋስ እንደሆነ የወልድም እስትንፋሱ ነውና» ብላል። ( ሃይማኖተ አበው ገጽ 328 ቍ. 58)።

በዚህ ለነገሥታት በላከው መልእክቱ በድጋሚ ሰለ መንፈስ ቅዱስ ሲጽፍ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ባሕርይ አባቱ በመለኮቱ ፍጹም ሲሆን ሰው በመሆኑ መንፈስ ቅዱስን ገንዘብ እንደ አደረገ ቢነገርም እርሱ ባመኑበት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንዳሳደረ አሰተውሉ፤ ፍጹማን ያደረጋቸው ሌላ አይደለም፤ የእርሱም የአባቱም እስትንፈስ መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ» ሲል አስረድታል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ 332)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አብና የእግዚአብሔር ወልድ መንፈስ እንደሚባል ሲመሰክር «እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» ብሏል። (ሮሜ 8፤9-10)

## ጥያቄ፤ መንፈስ ቅዱስን የተቃወሙ መናፍቃን እነማን ነበሩ?

መንፈስ ቅዱስን «ብዔል ዜቡል» ብለው የሰደቡ ፈሪሳውያንና ተከታዮቻቸው ነበሩ። ለእነርሱም ምንም ዓይነት ይቅርታ እንደማይደረግላቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦአል (ማቴ. 12፣31-33)። ህልውናውን የካዱ ሰዱቃውያን ይቅርታ የሌለው ፍርድ እንደሚጠብቃቸው የታወቀ ነው (የሐዋ.23፣ 8)።

መቅዶንዮስና ተከታዮቹ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በመካድ «ከአብ ከወልድ ያነሰ ነው» ብለው ስላስተማሩት ከዚህ አስጸያፊ ክሕደታቸው ይመለሱ ዘንድ በተደጋጋሚ ተጠይቀው አሻፈረን ስላሉም በ381 ዓ.ም በቁስጥንጥንያው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተወግዘው ከቤተ ክርስቲያን ተለይተዋል። የዚያው ጉባኤ አባላት የነበሩ ቅዱሳን አበውም መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን በማመን «ማሕየዊና ጌታ በሆነው ከአብ በሠረፀው በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን፤ ከአብና ከወልድ ጋራ በአንድነት እንሰግድለታለን፣ እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው» ብለው እውነተኛዋን እምነት ወስነው በአዋጅ አጽድቀዋል።

## ጥያቄ፤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስንት ናቸው?

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እጅግ ብዙ ነው። ይኸውም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድ መለኮት ዓለምን ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ፈጠረ። እግዚአብሔር አብ ሰማያትንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን ፈጠረ ሲባል፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ፈጠረ ማለት አይደለም። ሦስቱም አካላት አንድ አምላክ ነውና አብ ፈጣሪ፣ ወልድ ፈጣሪ፣ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ ይባላሉ እንጂ፣ ሦስት አምላክ፣ ሦስት ፈጣሪአይደሉም።

መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ፣ በገጽና በአካል በባሕርይ ፍጹም አምላክ ሲሆን፣ ከ አምላክነቱ ሳይናወጽ በየጊዜው በነቢያት እያደረ ትንቢት እንዲናገሩ አድርጎአል። ቅዱሳን ነቢ ያት የአካላዊ ቃልን ወደዚህ ኣለም መምጣትንና ሰው መሆን በልዩ ልዩ ምሳሌና ትንቢት ሊናገሩ የቻሉት በመንፈስ ቅዱስ ነው። ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ለመውለድ የቻለችው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው። ቅድስት ድንግል ማርያም «ንጽሕት እምን ጹሓን፣ ቅደስት እምቅዱሳን ወትረ ድንግል በክልኤ፣ ድንግል በኅሊናሃወድንግል በሥጋሃ» የም ትባለው መንፈስ ቅዱስ ከሦስት ግብር ስለጠበቃት ነው። ሦስት ግብራት (ሥራዎች) የተባሉትም፣ በማንኛውም ሰው የሚገኙ፣ የሚደርሱ «ሩካቤ ሥጋ፣ ዘርዕ፡ ለስሎተ ድንግልና፣ ማለት ክብረ ድንግልናን መተው» ናቸው። እነዚህ ሁሉ በእርሷ አልደረሱምና፤ በመንፈስ ቅዱስ ጠባቂነት ተ ጠብቃ ዘላለም ድንግል እንደ ሆነች ኖራለች፤ ትኖራለች።

አካላዊ ቃል ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ፤ አብ ከሰማያት፣ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ የባሕርይ ልጅነቱን ሲመሰክርለት፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ረቦ በታየ ጊዜ፣ አማናዊው ምስጢረ ሥላሴ በጉልህ ተገለጸ። መንፈስ ቅዱስ ለወል ደ እግዚአብሔር ክርስቶስ «በምስጢረ ኩነት» የባሕርይ ሕይወቱ ስለሆነ፣ ርኩሳን መናፍስትን ገንዘቡ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ አውጥቶአል (ማቴ. 12፣28)።

መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረፀ ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ የታወቀ ቢሆንም (ዮሐ. 15፣26) ለሐዋር ያት፣ ለቤተክርስቲያን፣ ለመላ ምእመናን አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ) ይሆን ዘንድ አካላው ቃል ከሙ ታን ተለይቶ በተነሣ በአምሳኛዉ ቀን ወደ ሰማይ ባረገ በአሥረኛው ቀን፣ መንፈስ ቅዱስን ለሐ ዋርያት ላከላቸው (የሐዋ. 2፣1-4)። ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው አርድእት መንፈስ ቅዱስን ተቀብ ለው፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ጌታና የዓለም መድኀኒት መሆኑን በግልጽ መሰከሩ። በቅ ዱስ ጴጥሮስና በሌሎች ሐዋርያት ስብከት በአንድ ቀን ሦስት ሺህ ሕዝብ በሌላው ቀን ከአም ስት ሺህ የሚበልጥ ህዝብ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የእግዚአብሔርቤተሰብ ሊሆን ቻለ ። ሐዋርያት በአጭር ጊዜ ውስጥ በርከት ያለውን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር መልሰው ቤተክርስ ቲያንን በስፋት ሊመሠርቱ የቻሉት መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር በመሆኑ ነው (የሐዋ. 2፣41 ፤ 4፣4)

ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ስላደረባቸው፣ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ሽ ባ ሆኖ የተወለደውንና ለብዙ ዓመታት በዚያው በሽታ ይሰቃይ የነበረውን ሰው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሊፈውሱት ቻሉ (የሀዋ.3፣1-10)። ቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት ጸጋ መን ፈስ ቅዱስ በሙላት ስላደረበት፣ ጥላው ያረፈባቸው በሽተኞች እንኳ ሳይቀሩ ይፈወሱ ነበር (የ ሐዋ.5፣15)።

ቅዱሳን ሐዋርያትና አርድእት መንፈስ ቅዱስ ስላደረባቸው ልዩ ልዩ ሕሙማንን የመፈወስ ኀይል ፣ ርኩሳን መናፍስትን ከልዩ ልዩ በሽተኞች ላይ የማስወጣት ሥልጣን፣ ሙታንን ለማስነሣት የ ሚያስችል አስደናቂ ኃይል ተሰጣቸው። ቅዱሳን ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው አርድእት የሰዎችን ኃጢአት ለማስተስረይና ይቅር ለማለት የሚያስችል ሥልጣነ ክህነት ያገኙት መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ ነው (ዮሐ.20፣21-23 ፤ የሐዋ.20፣28)

መንፈስ ቅዱስ አካሉ አንድ ነው። መንፈሰ ቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ ሲሆን ጸጋው ግን እ ጅግ ብዙ ነው።አንድ መንፈስ ቅዱስ በልዩ ልዩ ጸጋ የተለያየ መንፈሳዊ ስጦታ ለተለያዩ አገልጋ ዮች እንደሚሰጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል። «ለአንዱ ጥበብን መንገር በመንፈስ ይሰጠዋል። ለአንዱም በዚያው መንፈስ ዕውቀትን መናገር (ማወቅ) ይሰጠዋል። ለአን ዱ በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መንፈስየመፈወስን ስጦታ ለአንዱም ተአምራ ትን ማድረግ፥ ለአንዱም ትንቢት መናገር፥ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ል ዩ ዓይነት ልሳን (ቋንቋ) መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል። ይህን ሁሉ ግን ያ፥ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅደው ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል» (1ኛ ቆሮ.12፤ 4-11)።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አምላክነት አውቀው የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ከተቀበሉና ለሚቀበሉ ሰዎች ልዩ ልዩ ጸጋውን እንደሚያድላቸው ሐዋርያው ጥሩ አድርጎ ገልጾታል። ከሐዋርያው ሰባት መቶ ዓመት ቀደም ብሎ የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስም የአንዱ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በተለያየ መንገድ እንደሚሰጥ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ቃሉም ይህ ነው። «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፥ ከስሩም ቁጥቋጦ ያፈራል። የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል (ኢሳ.11፤ 1-3)

መንፈስ ቅዱስ መከፈል ሳይኖርበት፣ በአብና በወልድ በራሱም ፈቃድ ልዩ ልዩ ጸጋውን ለተለያዩ ሰዎች ሲያድል፣ እርሱ ራሱ እንደማይከፈልና ሀብቱም እንደማያልቅበት ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ሲመሰክር እንዲህ ብሎአል። «እንደሚሰጣቸው እንደ ሀብቱ መጠን ከእርሱ ይቀበሉ ዘንድ ከእነርሱም አንዱም አንዱን (እያንዳንዱን) የበቁ ያደርጋቸዋል፤ ሀብቱም ሁሉ ከእርሱ ከራሱ ይሰጣል፤ ከእርሱም ስለተሰጠው ለእርሱ ምንም ምን አይጐድለውም፤ እርሱ መቼም መች (ምን ጊዜም) ሕፀፅ (ጉድለት) የለበትምና። ፀሐይ በሰው ሁሉ ላይ እንዲያበራ ከእርሱም ሁሉ እያንዳንዱ በየአካላቸው ሙቀትን ብርሃንን እንዲቀበሉ ከእርሱ ሰለተሰጠው ሙቀት ብርሃን ምንም ምን እንዳይጐድለው መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሀብቱን ያሳድራል፤ ነገር ግን አይጐድልበትም፤ አይከፈልም» (ሃይማኖተ አበው ገጽ 114-115 ቍ. 47-48)።

በተጨማሪም ይህ ቅዱስ አባት ሰለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ከጻፈው መልእክት እጅግ ጠቃሚ የሆነውን ክፍል ከዚህ ቀጥለን ጠቅሰነዋል። «ሕያው እግዚአብሔር በማሳወቅ ሁሉን አዋቂ ያደርጋል። በነቢያት ቃለ ትንቢትን ይናገራል፤ በሕግ ጸንተው ላሉ ጥበብን ይገልጣል፤ ካህናትን ጻድቃን ያደርጋቸዋል፤ ለነገሥታት ኃይልን ይሰጣል፤ መከራውንም ለሚታገሱ ትእግሥትን ይሰጣል፤ እውነተኛ ሀብትን፣ ልጅነትን (የጸጋ ልጅነትን) ያድላል፤ ሙታንን ያስነሳል፤ እስረኞችን ይፈታቸዋል፤ ከኃጢአት ከጣዖት የተለዩትን በጥምቀት ዳግመኛ እንዲወለዱ (የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ) ያደርጋቸዋል፤ በእኒህና በሚመስላቸውም ላይ ይህን ያደርጋል» (ሃይማኖተ አበው ገጽ 115 ቍ. 49-50)።

መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች፣ ታጋሾች፣ ሃይማኖተኞች፣ ፍቅርን ምጽዋትን የሚወዱ፣ ጸሎተኞች፣ ርኅሩሆች ናቸው። ም~ንያቱም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ናቸውና» (ገላ. 5፤ 22-23 )።

ቅዱሳን ነቢያት ትንቢት ሊናገሩ የቻሉት መንፈስ ቅዱስ ሰላደረባቸው ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት የእግዚአብሔር መልእክተኞች በሆኑ መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው ሰዎች ነው (1ኛ ጴጥ. 1፤20-21)። ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚቀድሰ መንፈስ ቅዱስ ነው። ማንኛውም ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም (ዮሐ. 3፤5 )። ዮሐንስ መጥምቁ ለንስሐ በውኃ ያጠምቅ ነበር (ማቴ. 3፤11)። ጌታችን ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃል (ማቴ. 3፤11-12 ፤ ዮሐ. 1፤32-34)።

**ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ1991 ካሳተሙት የተወሰደ።**